# የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ዘዴ

## ማውጫ


| | ገጽ |
|---|---|
| 1. መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰጠውን ጥቅም ................ | 2 |
| 2. ጠቃሚ የሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ የምንባብ ክፍሎች አመራረጥ ................ | 3 |
| 3. የተማሪዎች ችግር ................ | 4 |
| 4. የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዓይነቶች ................ | 6 |
| 5. የመጽሐፍ ቅዱስን ምንባብ የመመርመር ዘዴ ................ | 8 |
| 6. በምንባቦች መካከል ያሉትን ግንኙነቶች የሚፈልግ ዘዴ ................ | 12 |
| 7. የጥቅሶች ማውጫ አጠቃቀም ................ | 13 |
| 8. መጽሐፍ ቅዱስን የመረዳት ዘዴ ................ | 14 |
| 9. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ምልክት የማድረግ ዘዴ ................ | 17 |
| 10. ንድፎችን የመንደፍ ዘዴ ................ | 19 |
| 11. የቃላት ጥናት ................ | 20 |
| 12. የመጽሐፍ ጥናቶች ................ | 22 |
| 13. ትምህርት ለማስተማር መዘጋጀት ................ | 23 |

# የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ዘዴ

## 1. መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰጠውን ጥቅም

ማቴ.4፡1-4፣ የሐዋ.17፡10-12፣ 2ኛ ጢሞ.3፡10-17።

### ሀ. የክርስቲያን የዕለት እንጀራ ነው፣ ማቴ.4፡4

ከእንጀራ ይልቅ ለሰውነታችን በጣም አስፈላጊ የሆነው ነገር ኢየሱስ ክርስቶስ በተፈተነበት ወቅት ለእግዚአብሔር ያሳየውን ዓይነት ታዛዥነት ማሳየት ነው። እርሱ ሰይጣን የሚጠይቀውን ነገር ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በማወዳደር ተቋቁሞታል። ነገር ግን እንደዚህ ዐማድረግ ሰው በእርግጥ በሕይወት ለመኖር ከእንጀራ በላይ ሌላ ነገር እንደሚያስፈልገው የሚናገር መመሪያ ደግሞ አውጥቷል።

ሰው መንፈሳዊ ፍጡር ስለሆነ ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ ግንኙነት ያስፈልገዋል። እኛ ግን ይህንን ትክክለኛ ግንኙነት ከእግዚአብሔር ጋር እንዴት እንደምናገኝ ብቻ በመጽሐፍ ቅዱስ አማካይነት ለመማር እንችላለን። የኢየሱስን ትምህርትና የእግዚአብሔር ቃል ስለ እርሱ የሚመሰክረውን የምናገኘው በመጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው፣ ዮሐ.5፡34-40።

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብና ማጥናት ያስፈልጋል።

### ለ. የክርስቲያን የዕለት መሪ ነው፣ መዝ.118/119/፡105

ጳውሎስ እና ሲላስ በተሰሎንቄ ወደ ምኩራብ በሄዱበት ወቅት አይሁዶች ሲቃወሟቸው በጣም ጥቂት ሰዎች አመኑ። ነገር ግን ሁለቱ ሰዎች ወደ ቤሪያ በሄዱና በሰበኩበት ወቅት አይሁዶች ጳውሎስ የተናገረው ነገር ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ይስማማ እንደሆነ ለመመልከት መጽሐፍ ቅዱሳቸውን ያጠኑ ነበር። መጽሐፍ ቅዱሳቸውንም ከማጥናታቸው የተነሳ ብዙ ሰዎች አመኑ። መጽሐፍ ቅዱስ መሪ ነው። አንድ መሪ እምነት እንዲጣልበት ስለ ትክክለኛው መንገድ እርግጠኛ መሆን አለበት። ሐሳቡን የሚለውጥ መሆን የለበትም። መጽሐፍ ቅዱስ ሃሣቡን በፍፁም አይለውጥም፣ መዝ.118/119/፡89።

### ሐ. ጽኑ መሠረት ነው፣ ኢሳ.40፡8

ጢሞቴዎስ ክርስቲያን የሆኑ እናትና ሴት አያት ነበሩት፣ 2ኛ ጢሞ. 1፡5። ከሕፃንነቱ ጀምሮ መጽሐፍ ቅዱስን አስተምረውታል፣ 2ኛ ጢሞ. 3፡15። መጽሐፍ ቅዱስ ለማንኛውም ሕፃን ለሕይወቱ ጽኑ የሆነ መሠረት ስለሚሰጥ ልጆቻቸውን ማስተማር የክርስቲያን ወላጆች ኃላፊነት ነው፣ ምሳ.22፡6።

አዲስ አማኞች እንደ ሕፃናት ናቸው። አማኞችን በቤ/ክ ውስጥ ማስተማር የቤ/ክ ሽማግሌዎች ኃላፊነት ነው፥ 1ኛ ጢሞ.4፡6።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጠቃሚ የሚሆንባቸውን መንገዶች አስተውሉ፥ 2ኛ ጢሞ.3፡16፤ ለማስተማር ለተግሳፅ፤ ለማስተካከል፤ ጽድቅን ለማለማመድ። የእግዚአብሔር ቃል ትክክለኛውን መንገድ ያሳየናል፤ የተሳሳተ ጎዳና ከያዝን ይገስፀናል፤ ስንስት ያስተካክለናል፤ እንዲሁም ወደ ቅዱስ ኑሮ ይወስደናል። ይህ የእግዚአብሔር እንጂ የሰው ቃል አይደለም። ለአዕምሮ የሚያስቸግር ውስብስብ ከመሆን ይልቅ ጥበብን ያሳየናል። አንድ ሰው ወደ ዩኒቨርስቲ በመሄድ አዋቂ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ይህ እርሱን ጥበበኛ ሊያደርገው አይችልም፥ ያዕ.3፡13-18 አንብቡና በሰይጣናዊው ብልሃትና በመለኮታዊው ጥበብ መካከል ያለውን ንጽጽር ልብ ብላችሁ ተመልከቱ።

## 2. ጠቃሚ የሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ የምንባብ ክፍሎች <u>አመራረጥ፥</u>

ኢሳ.53፥ የሐዋ. 9፡1-9።

መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ዓመታት ተጠብቆ ቆይቶ ለእኛ ደርሶናል። ይህንን መጽሐፍ ለማጥፋት ሙከራዎች ቢደረጉም የተሳካ ውጤት አላስገኙም። ለመጽሐፍ ቅዱስ ካላቸው ፍቅር የተነሳ ብዙ ሰዎች መከራ ሲቀበሉም አንዳንዶችም ሞተዋል። ኢዮአቄም የእግዚአብሔርን ቃል ለማጥፋት ያደረገውን ያልተሳካ ሙከራ በማስተዋል ተገንዘቡ፥ ኤር.36። ይህ መጽሐፍ እግዚአብሔር ራሱ ጠብቆ ያቆየው ስለሆነ በጣም ጠቃሚ መሆን አለበት። በተጨማሪ ጠብቆ ለማቆየት ከፍተኛ ዋጋ የሚጠይቅ ከሆነ እያንዳንዱ ገጽ ጠቃሚ መሆን ይኖርበታል። ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ሁለት ነገሮችን እንማራለን። እነርሱም እያንዳንዱ ገጽ ጠቃሚ መሆኑና በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ማንኛውም ነገር ተደግሞ የሚገኝ ከሆነ በጣም ጠቃሚ መሆኑ ነው። ጠቅላላ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ለእኛ የሚናገረው ቁም ነገር ቢኖረውም እንኳ አንዳንድ ክፍሎች በተለይ ጠቃሚ ናቸው። ታዲያ እነዚህን ክፍሎች እንዴት ልናውቃቸው እንችላለን?

ሀ. አንድ ታሪክ ከተደጋገመ በጣም ጠቃሚ ነው። የጳውሎስን መለወጥ በማስተዋል ተመልከቱ፥ ሐዋ.9፡1-9፥ 22፡1-11፥ 26፡12-18።

ለ. አንድ ጥቅስ በተደጋጋሚ ከተጠቀሰ ጠቃሚ መሆን ይኖርበታል፥ ለምሳሌ:- ኢሳ.53፥ ዮሐ.12፡38፥ ሮሜ 10፡16፥ ማቴ. 8፡17፥ ማቴ. 26፡63፥ ማቴ. 27፡12-14፥ 1ኛ ጴጥ.2፡24፥ የሐዋ.8፡32-35።

ሐ. አንድ ታሪክ ከሌሎች ጋር ሲነፃፀር ብዙ ሥፍራ ከተሰጠው ጠቃሚ ነው። ለምሳሌ:- የአብርሃም ሕይወት፥ ዘፍ.11፡26-25፡11። ሌላው ምሳሌ ደግሞ የሕማማቱ ሳምንት ዘገባ ነው። ክርስቶስ ለኖረባት የመጨረሻ ሳምንት የተሰጡትን ምዕራፎች ብዛት ከተገነዘባችሁ በኋላ ለተቀረው ከ30 ዓመታት ለሚበልጠው የክርስቶስ ሕይወት

ከተሰጠው ሥፍራ ጋር አወዳድሩት። የኢየሱስ ክርስቶስ የልጅነት ወቅት ብዙ ትኩረት እንዳልተደረገበት አስተውሉ።

## 3. የተማሪዎች ችግር

ማንኛውንም ዓይነት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ከማዘጋጀቱ በፊት ጥናቱን የሚያጠኑት ሰዎች ያለባቸውን ችግር መመልከት በጣም አስፈላጊ ነው። ሕፃናት ከአዋቂዎች እና ወንዶች ከሴቶች የተለየ ትምህርት ያስፈልጋቸዋል። በተጨማሪ ትክክለኛውን ትምህርት ለማስተማር የተለያዩ መንገዶች ስላሉ ተስማሚ የሆነው የማስተማሪያ ዘዴ መመረጥ ይኖርበታል። አንዳንድ የአጠናን ዘዴዎች ለጥናት ከሚያስፈልጓቸው ነገሮች ጋር ከዚህ በታች በዝርዝር ቀርበዋል።

### ሀ. የግል የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

ጠቅላላውን መጽሐፍ ቅዱስ ሥርዓት ባለው አካኋን ለማንበብ መከራ ማድረግ ያስፈልጋል። አንዳንድ አስቸጋሪ የሆኑ የምንባብ ክፍሎችን ለመረዳት አዲሱን የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ ተጠቀሙ። የብሉይ ኪዳን እና የአዲስ ኪዳን መከፈቻ ደግሞ መጻሕፍቱንና ዓላማዎቻቸውን ለመገንዘብ ይረዳል።

### ለ. የሰንበት ትምህርት ቤት ወይም ሳምንታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል

ብዙ ቤ/ክርስቲያናት በአሁኑ ወቅትም እንኳ የአማኞችንና የማያምኑ ሰዎችን ልጆች የመጽሐፍ ቅዱስን መመሪያ የሚያስተምሩበት ቋሚ ክፍለ ጊዜ የላቸውም። መምህሩ አስበ እንዲያው የመሰለውን ለእያንዳንዱ ሳምንት ያዘጋጃል። የኢየሱስ ክርስቶስን የተለያዩ ታሪኮችና የአብርሃም፣ ሙሴ፣ ኤልያስ፣ ኢዮስያስ፣ ዳዊት ወዘተ... የመሳሰሉትን አንዳንድ የብሉይ ኪዳን ታሪኮች ይመርጣል። አሁን ጥናት በዘዴ የተባሉት መጻሕፍት ለሳምንታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ተዘጋጅተዋል። እነርሱም 3 የሕፃናትና አንድ የአዋቂ ናቸው። እያንዳንዱ መጽሐፍ 52 ትምህርቶች ሲኖሩት ለሕጻናትና ለዐዋቂዎች አስፈላጊ የሆነ ትምህርት ይሰጣል።

### ሐ. የአይሁድ ስብሰባዎች

አንድ ሰው ለ3 ወራት በየእሁዱ እንዲሰብክ ማድረግ የሚያስገኘው ጥቅም ሰውየው ተከታታይ የሆኑ መልዕክቶችን ሊያቀርብ ይችላል። በየሳምንቱ የተለያዩ ሰዎች ቢሰብኩ ውጤቶቹ በአንድ ወይም በሁለት የትምህርት ዓይነቶች ላይ የሚቀርቡ ብዙ መልዕክቶች ሊሆኑ ይችላሉ። ስብሰባው የቅዱስ ቁርባን አገልግሎት ከሆነ መልዕክቱ ስለ ፍርድ ወይም በአማኞች ውስጥ ስለሚገኝ ኃጢአት ሊሆን ይችላል፣ 1ኛ ቆሮ. 11፡27-37፣ የሐዋ. 5፡1-11። በአገልግሎቱ ወቅት የማያምኑ ሰዎች ካሉ መልዕክቱ የክርስቶስን መስቀል የሚያቀርብ መሆን አለበት፣ 1ኛ ቆሮ.2፡1-5።

መ. የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት

በመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት መምህሩ ምን ማስተማርና እያንዳንዱን የትምህርት ዓይነት የሚያስተምርበትን የጊዜ ርዝመት የሚነገረው ስርዓተ ትምህርት እንዲኖር ያስፈልጋል። አንድ ሰባኪ የማቴዎስን ወንጌል ለማስተማር አምስት ዓመት ሊፈጅበት ወይም አንድ ሳምንት ብቻ ሊያጠፋ ይችላል። መልዕክቱና እንዲፈጅ የተወሰነለት ጊዜ መወሰን ይኖርበታል። ለሮሜ፣ ለኤፌሶን እና ለሌሎቹም መጻሕፍት ለዕለት ትምህርት እንዲያገለግሉ በክፍል በክፍል የሚመድባቸውን የማስተማሪያ መምሪያ ተጠቀሙ፤ ደግሞ ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያዎችን አገናዝቡ። ትምህርቱን ለማሻሻል በየዓመቱ በሥርዓተ ትምህርቱ ውስጥ አዳዲስ መጻሕፍት ይጨመራሉ። አዳዲስ ማስተማሪያዎቹ ለመምህራን ስለሚያስተምሩት ነገር አዲስ ዕውቀት እንዲኖራቸው ይረዱአቸዋል። የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት ትምህርት ልማዳዊ መሆን የለበትም። ስለምናስተምራቸው የትምህርት ዓይነቶች አዳዲስ ዕውቀት ለማግኘት ዘወትር የምናጠና መሆን ይገባናል። በመንፈሳዊ ሕይወታችን ንቁ መሆን ያስፈልገናል፤ በተጨማሪ ትምህርት የሚሰጥባቸው ክፍሎች የምናስተምራቸውን ተማሪዎች ስሜት የሚያረኩና የሚያነቃቁ እንዲሆኑ አድርጓቸው።

በተጨማሪ ከእነዚህ መደበኛ ስብሰባዎች ሌላ አልፎ አልፎ ንግግር እንድታደርጉ የምትጠየቁበቸው የተለዩ ስብሰባዎች ይኖራሉ። በእነዚህ ዓይነት ስብሰባዎች የሚመጡት ሰዎች እንደ ወትሮው በቤተ ክርስቲያኒቱ ስብሰባ ላይ ለመካፈል የሚመጡ ስለማይሆኑ ጥንቃቄ የተሞላበት ዝግጅት ያስፈልጋል።

ከእነዚህ ልዩ ዝግጅት እንድታደርጉላቸው ከሚያስፈልጋችሁ ስብሰባዎች መካከል ጥቂቶቹ ከዚህ በታች ቀርበዋል።

ሠ. ሠርግ

አስተማሪው ለምን ክርስቲያን መፋታት እንደማይፈቀድለት ቢረዳ በጣም ጠቃሚ ነው። ይህ በጋብቻ እና በክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ግንኙነት መካከል ጎን ለጎን የሚሄድ ነገር ነው። ለሰዎች ስለ እግዚአብሔር ፍቅርና እርሱ ለሕዝቡ ስላለው ታማኝነት ለመንገር ግሩም የሆነ አጋጣሚ ነው። ትምህርተ ክርስትና 3ኛ ስለ ጋብቻ ትምህርት ያቀርባል።

ረ. የቀብር ሥነ ሥርዓት

የቀብሩ ሥነ ሥርዓት የአማኝ ከሆነ መልዕክቱ በእርግጠኝነት ላይ የሚያተኩር ይሆናል። የሞተው ሰው በሳጥኑ ውስጥ ሳይሆን በእግዚአብሔር ዘንድ ነው። የሞተው ሰው አማኝ ካልሆነ ዘመዶቹ ራሳቸውን ተስፋ ሊሰጣቸው ለሚችለውና እነርሱን ለማጽናናት ለሚሻው ለእግዚአብሔር እንዲሰጡ ጥሪ ለማድረግ ግሩም የሆነ ዕድል ታገኛላችሁ። ዮሐ.11፤ የዓልዓዛርን መነሳት ወይም ሉቃስ 7፡11-16፤ በናይን ከተማ የነበረችው ባልዋ የሞተባት ሴት ታሪክ ልትጠቀሙ ትችላላችሁ።

ሰ. ታላቅ ስብሰባ /ኮንፍራንስ/

ይህ ታላቅ ስብሰባ የታቀደው ለማን እንደሆነ መረዳታችሁን አስቀድማችሁ እርግጠኛ ሁኑ። ለአማኞች የተዘጋጀ ታላቅ ስብሰባ ነው? ወንጌላዊ ስብሰባ ነው? ይህ ታላቅ ስብሰባ ልዩ የሆነ አቢይ ዓላማ አለው?

ዘወትር በታላቅ ስብሰባው አጋማሽ ላይ የመጀመሪያው ቡድን የተቀሩት የቤተሰቡ አባላት መጥተው እንዲሰሙ ለማድረግ ወደ ቤቱ ሲመለስ በአጠቃላይ ትልቅ ለውጥ ይኖራል።

ሸ. የቤት ውስጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት።

- እንደገና የምታስተምሩትን ቡድን እወቁ! ምን ያህል የመጽሐፍ ቅዱስ ዕውቀት አላቸው? የእግዚአብሔርን ቃል በማንበብና በመረዳት ረገድ ያላቸው ችሎታ ምን ያህል ነው?

እንደዚህ ዓይነት ክፍል በተቻለ መጠን የውይይት ክፍል መሆን አለበት። መሪው የእግዚአብሔርን ቃል ለዕለት ችግሮቻቸው እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው ለመምራት መከራ ማድረግ ይኖርበታል።

የዕድገት በጽሒፈት ማስተማሪያዎችና ትምህርተ ክርስትና ለእንደዚህ ዓይነት ክፍል ጥሩ ናቸው።

## ለክፍል ወይም ለቤት ሥራ የቀረቡ ሐሳቦች

1. በአዲስ ኪዳን ውስጥ አብርሃምን የሚመለከቱትን ጥቅሶች በማስተዋል ተገንዘቡ። ጥቅሶቹን በሙሉ ወይም ግምገማ በማድረግ እያንዳንዱ ምንባብ ስለ አብርሃም ምን እንደሚልና እንደሚያስተምር ለማወቅ እንዲረዳችሁ አድርጉ።
2. ኤር.36ን አንብባችሁ ከዚህ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።
   ሀ/ ጥቅልሉ መጽሐፍ እንዲፃፍ ያዘዘው ማን ነው?
   ለ/ ቃላቱን በትክክል የገለበጠው ማን ነው?
   ሐ/ መጽሐፉ ሲነበብ የሰማው ማን ነው?
   መ/ ጥቅልሉን መጽሐፍ ያጠፋው ማን ነው? ከዚያ በኋላ ምን ተደረገ?
   ሠ/ ይህ ምዕራፍ ስለ እግዚአብሔር ቃል ምን ያስተምረናል? ማቴ.24፡35።

## 4. የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዓይነቶች

አንድ የትምህርት ዓይነት በምንመርጥበትና ለማስተማር ላቀድነው ነገር ጥናት በምናደርግበት ወቅት እነዚህን ጥያቄዎች መጠየቅ ይኖርብናል፡- ተማሪዎቹ እነማን ናቸው? ወይም አድማጮቹ እነማን ናቸው? የማስተምረው ስንት ክፍለ ጊዜ ነው? በእያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ የሚኖረኝ ሰዓት ምን ያህል ነው? እነዚህ ነገሮች የምናስተምረው የትምህርት ዓይነትና የምንጀምረው የጥናት ዓይነት ምን መሆን እንዳለበት ይወስናሉ።

ልናካሂዳቸው የምንችላቸው የጥናት ዓይነቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ. በቀጥታ ከዘፍጥረት እስከ ራዕይ መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት።

ይህ የሚቻለው ለግል የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ነው። ሆኖም መጻሕፍቱ የተቀመጡት በተጻፉበት ጊዜ ቅደም ተከተል እንዳልሆነ አስተውሉ። 1ኛና 2ኛ ሳሙኤልንና ነገሥትን በድጋሚ ያቀርባሉ፣ የሐዋርያት ሥራ ከሉቃስ ቀጥሎ መቅረብ ይኖርበታል፣ ኢያሱ ከዘፀዓት በኋላ ቢነበብ እጅግ የተሻለ ነው።

ለ. በአንድ መጽሐፍ ላይ የሚደረግ ጥናት

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙት መጻሕፍት ርዝመታቸው የተለያየ ነው። 150 መዝሙሮች፣ ኢሳይያስ 66 ምዕራፎችና ኤርምያስ 52 ምዕራፎች አሏቸው። አብድዩ፣ ፊልሞና፣ 1ኛና 2ኛ ዮሐንስና ይሁዳ አንድ አንድ ምዕራፍ ብቻ አሏቸው። አንድ መጽሐፍ ለማጥናት ካቀድን በመጀመሪያ ማድረግ ያለብን መጽሐፉን በቀጥታ ያለማቋረጥ ማንበብ ነው። መጽሐፉ አጭር ከሆነ መጽሐፉን መልሶ መላልሶ ብዙ ጊዜ ማንበብ ይገባል። እንደ ዘፍጥረት ያለ ረጅም መጽሐፍ ከሆነ በማንበብ ላይ እንዳለን ዋና ዋናዎቹን ክፍሎች መመዝገብና አንድ በአንድ በተራ ማጥናት አለብን።

ሐ. የሰው ሕይወት ታሪክ

አድማጮች እንደዚህ ዓይነት ጥናት በጣም ይማርካቸዋል። የኖህን ታሪክ አጥንታችሁ ስለ እርሱ የምትረዱትን ነገር መዝግቡ፡- አባቱ ላሜክ ነበር። ሴም፥ ካምና ያፌት የተባሉ ሦስት ልጆች ነበሩት። በእግዚአብሔር ዐይን ሞገስ አገኘ። ጻድቅ ሰው ነበር። ከትውልዱ መካከል ፍጹም ነበር፣ «ፍጹም ነበረ» ማለት ምን ማለት ነው? ከእግዚአብሔር ጋር ተመላለሰ። የእናንተን ትምህርት የሚመለከቱ ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች በጥንቃቄ አንብቡ። ለምሳሌ ኖህ በኢሳ.54፡9፥ በሕዝ.14፡14፥ በማቴ.24፡37፥ በዕብ.11፡7፥ በ1ኛ ጴጥ.3፡20፥ በ2ኛ ጴጥ.2፡5ና በ1ኛ ቆር.1፡4 ውስጥ ተጠቅሷል።

መ. የቃላት ጥናት

እንደዚህ ዓይነት ጥናት ለማድረግ ጥቅስ ማውጫ ያስፈልገናል። ልናጠናቸው የሚገቡን ጠቃሚ ቃላት፥ ስርየት፣ ቤዛ፣ ፍርድ፣ ትንሳኤ፥ ሞትና ፀጋ ናቸው። የእያንዳንዱን ምንባብ ዋና ትምህርት ስንፈልግና ስንመዘግብ የምናገኘውን ቃል በብዙ ማመሳከሪያዎች ማገናዘብ ይገባናል። ቃሉ በዘመናዊ አነጋገር እንዴት በጥቅም ላይ እንደዋለ ጠይቁ። ለምሳሌ አመነ ማለት ማመን ማለት ሲሆን በተጨማሪ ንሥሐ መግባት ማለት ነው።

ሠ. መልከዓ ምድራዊ ሥፍራ

የተለየ ዓይነት የቃላት ጥናት ስለ ከተማ ወይም አገር የሚደረግ ነው፣ ለምሳሌ ቃዴስ፥ ባርኔያ፥ ዳን፥ ግብፅ፥ ኢትዮጵያ፥ ኢየሩሳሌም።

ረ. አርዕስታዊ ጥናትና ትምህርተ ሃይማኖት

አርዕስታዊ ወይም የአንድ ትምህርት ጥናት በጣም አስቸጋሪ ነው። ለእንደዚህ ዓይነት ጥናት ምን ዓይነት ምንባቦችን ማንበብ እንዳለብን የሚያሳዩን በትምህርቱ ላይ የሚያተኩር መጽሐፍ ያስፈልገናል። ክርስቶስ በማደሪያ ድንኳን፣ የጳውሎስ ሕይወትና ትምህርቱ፣ ትምህርተ ሃይማኖት 1ኛ 2ኛና 3ኛ የመሳሰሉት መጻሕፍት ጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ።

እነዚህ የተለያዩ የጥናት ዓይነቶች ሁሉ ከዚህ በታች በሚገኙ ሦስቱ ቡድኖች በአንዳቸው ውስጥ ሊጠቃለሉ ይችላሉ። ቡድኑ ለጥናት በምንመርጠው ማስተማሪያ መጠን ይወሰናሉ።

1ኛ አጭር ምንባብ፦

በጣም ጥቂት ጥቅሶችን ብቻ የወሰድን ከሆነ ጠለቅ ብለን ልንመለከታቸው እንችላለን። እያንዳንዱን ቃል ልናጠና፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሌላ ሥፍራ የሚገኙትን ማመሳከሪያ ጥቅሶች ልናነብና ትርጉሙን ለማብራራትና ለማስፋት ሌሎች ጥቅሶችን ልንጠቀም እንችላለን።

2ኛ አንድ ምዕራፍ ወይም መጽሐፍ፦

በእንደዚህ ዓይነት ጥናት ማጥናት የምንችለው የአጠቃላዩ ክፍል ዋና ዋና ክፍሎችና ልናስተምርም የምንችለው ዋና ዋናዎቹን ትምህርቶች ነው። ለዚህ ዓይነት ጥናት የሚረዱ ብዙ መጽሐፎች ይገኛሉ፣ ለምሳሌ ኢያሱ፣ 1ኛ ዮሐንስ፣ ኤፌሶን።

3ኛ አጠቃላይ ጥናት፦

አጠቃላይ ጥናት የመረጥን ከሆነ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ምዕራፎችን ማንበብና የአነበብነውን ነገር መገምገም ቢያስፈልግም እነዚህ ጥናቶች በጣም የሚጠቅሙት መጽሐፍ ቅዱሳቸው በሚገባ ላልተረዱት አዲስ አማኞች ነው። ክርስቲያን መማር የሚገባው አጫጭር ክፍሎችን ብቻ ሳይሆን ነገር ግን የአይሁዶችን ታሪክ፤ የክርስቶስን ሕይወት፤ የጳውሎስን ሕይወትና ትምህርቱ የዓለምን ፍጻሜና ነቢያትን የመሳሰሉ የመጽሐፍ ቅዱስ አጠቃላይ ይዘቶችንም ማወቅ ይገባዋል።

ጠቅላላው መጽሐፍ ቅዱስ እርስ በእርሱ እንዴት እንደሚስማማ ስለምንመለከት እንደዚህ ዓይነቱ ጥናት በጣም የሚያነቃቃ ነው። ለእንደዚህ ዓይነት ጥናት የሚረዱ መጻሕፍት አሉ። ለምሳሌ የብሉይ ኪዳን መክፈቻ፣ የአዲስ ኪዳን መክፈቻ የጳውሎስ ሕይወትና ትምህርቱ።

## 5. የመጽሐፍ ቅዱስን ምንባብ የመመርመር ዘዴ

ሀ. የምንባቡ የአጻጻፍ ዘይቤ ጠቃሚ ነው

ታሪክን በምንመለከትበት ተመሳሳይ መንገድ ግጥም ወይም ምሳሌዎችን ለመመልከት አንችልም።

1. ታሪካዊ ምንባቦች

የእስራኤል ነገሥታት ታሪክና የጳውሎስ መርከብ መሠበር ዘገባ ቀላል ለሆኑ ታሪክ ጥሩ ምሳሌዎች ናቸው።

በእንደዚህ ዓይነት ትምህርት ውስጥ ድርጊቱ መቼ እንደተፈጸመ መጠየቅ ጠቃሚ ነው። በድርጊቱ ውስጥ የተጠቀሱትን ነገሥታትን ወይም ነቢያት ስም መገንዘብ አስፈላጊ ነው። የአዲስ ኪዳን ታሪካዊና ባሕላዊ መሠረቶች የተባለ መጽሐፍ በብሉይና በአዲስ ኪዳን መካከል ስላለው ታሪክ ይገልጻል።

2. ትምህርተ ሃይማኖት ምንባቦች

ትምህርተ ሃይማኖት ምንባቦችን ስናጠና መቼ የሚለውን መረዳት ጥቅሙ በጣም ያነሰ ሲሆን ምንባቦቹ ለምን ተጻፉ የሚለውን ግን ማወቅ በጣም ጠቃሚ ነው። የገላትያን መልዕክት ለመረዳት የገላትያ ክርስቲያኖች ወደ ወግ አጥባቂነት ወደ ኋላቸው እንደተመለሱና ጳውሎስም የጻፈላቸው በዚህ ምክንያት መሆኑን ማወቅ በጣም ጠቃሚ ነው። ሆኖም ታሪካዊውንና ባሕላዊውን መሠረት መረዳት ትምህርቱ ያስፈለገው ለምን እንደነበር ያስረዳል። የጳውሎስ ሕይወትና ትምህርቱ፥ የአዲስ ኪዳን ታሪካዊና ባሕላዊ መሠረቶች ተመልከቱ።

3. የግጥም ምንባቦች

መዝ.103/የምናጠና ከሆነ የአይሁድን ግጥም ሁለት ገጽታ ልንገነዘብ እንችላለን። አንዱ ድግግሞሽ ሲሆን ሌላው ንጽጽር ነው።

መዝ.103 /104/፡7፡- በመጀመሪያው መስመር ላይ «ከዘለፋህም» የሚለው ቃል በ2ኛው መስመር ላይ «ከነጎድጓድህም ድምፅ» ከሚለው ሐረግ ጋር ትርጉማቸው ተመሳሳይ ነው።

በመጀመሪያ መስመር ላይ «ይሸሻሉ» የሚለው ቃል በ2ኛው መስመር ላይ «ይደነግጣሉ» ከሚለው ቃል ጋር ትርጉማቸው አንድ ዓይነት ነው።

ዳዊት በተጨማሪ እንዲህ ትላል፡- «ብርሃንን እንደ ልብስ ለበስህ! ሰማይንም እንደ መጋረጃ ዘረጋህ! » እነዚህ ጥቅሶች የሚናገሩት ሐሳብ ሰማይ መጋረጃ ነው የሚል አይደለም ወይም ነፋስ እውነተኛ ክንፍ የለውም። የምናነበው ነገር ግጥም ነው።

### 4. ምሳሌዎች

በምሳሌዎች ውስጥ ቁልፍ የሆነው ሃሳብ መመሳሰል ነው። የሚኖረን ተመሳሳይነት እንጂ ፍጹም የሆነ አንድነት አይደለም። ለመንፈስ ቅዱስ የተሰጠውን ገለፃ አስተውሉ። እርግብ ይመስላል፣ ሉቃ.3፡22።

ኑሱስና እሳት ይመስላል፣ የሐዋ.2፡1-3።

ኢየሱስ መንግሥተ ሰማያት ይህንን ትመስላለች የሚሉ ብዙ ምሳሌዎችን አስተምሯል። በማቴ.13፡1-52 ውስጥ 7 ምሳሌዎች ይገኛሉ። የእያንዳንዱ ምሳሌ ዋና ትምህርት ምንድነው?

### 5. ትንቢት

ትንቢቶች በሁለት ክፍሎች ሊከፈሉ ይችላሉ። አንዳንዶቹ ወዲያው በሚፈጸሙ ድርጊቶች ላይ የሚያተኩሩ ናቸው። ሌሎቹ ደግሞ ወደፊት ራቅ ካለ ጎዜ በኋላ በሚፈጸሙ ድርጊቶች ላይ ያተኩራሉ። ኤሊያስ ምንም ዝናብ እንደማይዘንብ ተነበየ፣ 1ኛ ነገ.17። ሚክያስ የአክዓብን መሸነፍ ተነበየ፣ 1ኛ ነገ.22።

ዳንኤል ግን ስለ ዓለም ፍጻሜ ትንቢት ተነበየ፣ ዳን.9፡24-27።

ለቅርብና ለሩቅ ጊዜ ድርጊቶች ሊጠቀሱ የሚችሉ አንዳንድ ትንቢቶችም አሉ። በኢሳይያስ 7 ውስጥ ስለ አንዲት ወጣት የተነገረው ትንቢት የሚጠቀሰው በሶሪያው ንጉስ በረአሶንና በእስራኤል ንጉስ በፋቁሔ በሁለቱም ዘመነ መንግሥት ትኖር ለነበረች ሴት ሲሆን ነገር ግን በተጨማሪ ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እናት ለድንግል ማርያምም ጭምር ነው፣ ማቴ.1፡23።

ለ. በምንባቡ ውስጥ የሚገኙት ቁልፍ ቃላት ጠቃሚ ናቸው

### 1. የተደገሙ ቃላት

የእግዚአብሔርን ቃል በምናጠናበት ጊዜ ማንኛውም ቃል ጠቃሚ ነው፣ ነገር ግን ቃላት የተደጋገሙ ከሆነ በተለይ ጠቃሚ ናቸው። እንደ ቅዱስና ወይራ የመሳሰሉት ቃላት ከተደገሙ በጥንቃቄ ትኩረት ሊደረግባቸው ይገባል።

### 2. ያልተለመዱ ቃላት

ከዚህ በፊት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያጋጠማችሁ መሆናቸውን ማስታወስ ያቃታችሁን ቃላት በምታገኙበት ወቅት በመጀመሪያ ልታደርጉ የሚገባችሁን ነገር ትርጉማቸው ምን እንደሆነ ማወቃችሁን እርግጠኞች መሆን ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ተጠቀሙ።

3. የቃላቱ ሰዋሰው

በአማርኛ የአንድ ምንባብን ሰዋሰው በምናጤንበት ጊዜ በሚገባ እንዲገባን ከተፈለገ ታላቅ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። የግሱ ባለቤት ያልተጠቀሰባቸውን ምንባቦች የተለየ ትኩረት አድርጉባቸው። ደግሞ ባለቤቱን በትክክል ማወቃችሁን እርግጠኞች ሁኑ።

የሐዋ.2፡25-28ን በጥንቃቄ አጥንታችሁ ስለ ዳዊት፥ የተባለውና ስለአብና ስለወልድ የተጠቀሰው ምን እንደሆነ አስተውሉ። ተውላጠ ስሞችን በምናገኝበት ጊዜ ዘወትር የተጠቀሱት ለማን እንደሆነ ማወቅ ጠቃሚ ነው። የአዲስ ኪዳን አዲስ ትርጉም ተመልከቱ።

ስሞችን በምናገኝበት ጊዜ ዘወትር ነጠላ ወይም ብዙ መሆናቸውንና ባለቤት ወይም የግሥ ተሳቢ መሆናቸውን መገንዘብ ጠቃሚ ነው። በተጨማሪ ስሞች እንዴት እንደተገለጹ ተገንዘቡ። በዮሐ.3፡16 ውስጥ አንድያ የሚለው ቃል ትርጉም ምንድነው?

4. በቃላት መካከል የሚኖሩ ዝምድናዎች

የአንድ ቃል ትርጉም የሚወሰነው በሚገኝበት ዓረፍተ ነገር አማካይነት ነው። የአንድ ዓረፍተ ነገር ትርጉም የሚወሰነው በአካባቢው ባሉ በሌሎች ዐረፍተ ነገሮች ነው። የአንድ ዐረፍተ ነገርን በተለይም ርጅም ከሆነ አጠቃላይ ክፍሉን መረዳት በጣም ጠቃሚ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ሲጠና አንድ ጥቅስን ከመተንተን ይልቅ ጠቅላላውን ምንባብ ማንበብ በጣም ጠቃሚ ነው። የማንኛውንም ረጅም ዓረፍተ ነገር አሠካከ መረዳት ጠቃሚ ነው። ማር. 8፡38ን በማስተዋል ተገንዘቡ። ሰው የሚያፍረው ለምንድነው? ክርስቶስ የሚመጣው እንዴት ነው? የሚመጣው ከማን ጋር ነው? ባፈሩት ሰዎች ላይ ምን ያደርግባቸዋል።

አንድ ረጅም የሆነን ዓረፍተ ነገር ለመረዳት ዘወትር እንደገና ዓረፍተ ነገሩን መጻፍ ጠቃሚ ነው። በአዲሱ የአዲስ ኪዳን ትርጉም ውስጥ ይህ ዓረፍተ ነገር የተጻፈው እንዴት እንደሆነ ተመልከቱ። ቃላቱ ወይም ደግሞ ቢያንስ ትርጉማቸው አልተለወጠም፤ አብዛኛውን ጊዜ አረፍተ ነገሩ የሚቀናጀው በዚህ መልክ ነው።

- ስለ አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ጥያቄዎችን መጠየቅ። ከዚህ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ሁሉ ለማንኛውም ዓይነት የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ልትጠይቁ አትችሉም፤ ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ሲጠና ቅዱስ ምንባብ ልትጠይቁ አትችሉም፤ ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ሲጠና እነዚህ ጥያቄዎች ብዙዎቻቸው መጠየቅ ይኖርባቸዋል።
    1. ይህንን የጻፈው ማን ነው ወይም ይህንን የተናገረው ማን ነው?
    2. ይህ ነገር የተጻፈው ወይም የተነገረው መቼ ነው?
    3. ይህ ነገር የተጻፈው ወይም የተነገረው ለምንድነው?
    4. ይህ ነገር የተጻፈው ወይም የተነገረው ለማን ነው?
    5. ይህ ነገር ስለተጻፈ ወይም ስለተነገረ ምን ተፈጸመ?

ነህምያ 6፡5-9 አንብባችሁ እነዚህን አምስት ጥያቄዎች በዚህ ሥፍራ በመጠቀም መልስ ስጡ።

## 6. በምንባቦች መካከል ያሉትን ግንኙነቶች የመፈለግ ዘዴ

ሀ. አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ በአንድ ምዕራፍ ውስጥ ቢቆምም እንኳ አብዛኛው ጊዜ ከሚቀጥለው ምዕራፍ ጋር የተያያዘ ነው። አንዳንድ ጊዜ የሚቀጥለውን ምዕራፍ ትርጉም በሚገባ መረዳት የሚቻለው የቀደመውን ምዕራፍ እንደገና በመመልከት ብቻ ነው። ይህ በተለይም በሮሜ መልዕክት ውስጥ እውነተኛ ሆኖ እናገኘዋለን። እንግዲህ በሚለው ቃል ስንት ምዕራፎች እንደሚጀምሩ አስተውሉ። ይህ የሚያሳየን ሁለቱ ምዕራፎች የተያያዙ መሆናቸውን ነው። የሚከተሉት በአማርኛ ምንባቦችን ለማያያዝ ከምንጠቀምባቸው ቃላት መካከል ጥቂቶቹ ናቸው:- ና፤ ም፤ ስለዚህ፤ እንግዲህ፤ በኋላ፤ ወዲያውም፤ ነገር ግን፤ ሆኖም።

ማር. 9፡1-13ን አንብባችሁ የምታገኙአቸውን ዓረፍተ ነገር አያያዥ ቃላት አስምሩባቸው። ማር.1 አንብባችሁ ወዲያውም የሚለውን ቃል ስታገኙ ምልክት አድርጉበት። በተጨማሪ በአጠቃላይ በዚህ ወንጌል ውስጥ የሚገኘው እንዴት እንደሆነ ተገንዘቡ።

ለ. አንዳንድ ጊዜ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ከሌላው ምንባብ ጋር የተያያዘው በቃል ሳይሆን ነገር ግን በተመሳሳይ ሃሳብ ነው። የአንድ ትምህርት አቢይ ዓላማ የሚያያዘው እንዴት እንደሆነ ተገንዘቡ።

በሉቃስ 15 ውስጥ

-አንድ በግ ጠፋ...ከመቶዎቹ መካከል አንዱ ብቻ ነው።
-አንድ ሳንቲም ጠፋ...ከአሥሩ መካከል አንዱ ብቻ ነው።
- አንድ ልጅ ጠፋ...ከሁለቱ መካከል አንዱ ብቻ ነው።

በ2ኛ ሳሙ.15 ውስጥ ናታን ስለ አንዲት በግ የተናገረው ምሳሌ የሚጠቁመን ወደ ኋላ ተመልሶ ዳዊት በምዕ. 11 ውስጥ ከቤርሳቤህ ጋር የፈፀመውን ኃጢአት ነው።

በ1ኛ ቆሮ.12፤13 እና 14 ሦስቱን ምዕራፎች ያያያዛቸው የመንፈስ ቅዱስ ሥጦታ በተለይም ደግሞ በልሳኖች የመናገር ሥጦታ ነው። በሦስቱ ምዕራፎች ውስጥ ስለ ሥጦታ የሚያብራራ ቃል ሲያጋጥማችሁ አስምሩበት። ጳውሎስ ማንኛውም ሥጦታ ፍቅር ካልተጨመረበት ጥቅመ ቢስ መሆኑን ያስተምራል። ብዙ ጊዜ ልሳኖች ፍቅር በማይታይበት መንገድ በጥቅም ላይ ሲውሉ ልዩነትን ይፈጥራሉ።

ሐ. የምታጠኑት ምንባብ ምናልባት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሌላ ሥፍራ ከሚገኙ በአንድ ዓይነት ትምህርት ላይ ከሚያተኩሩ ምንባቦች ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል። ከብሉይ ኪዳን የተጠቀሰ ማንኛውም ጥቅስ መመልከት በተለይ ጠቃሚ ነው።

ዮሐ. 3፡14ንና ስለ ምድረበዳው እባብ የሚያመለክተውን ዘኁ.21ን በማስተዋል ተገንዘቡ።

ማቴ.12፡38-42ና ስለ ዮናስ፥ ንነዌና የደቡብ መንግሥት የሚያመለክቱትን ክፍሎች ትኩረት አድርጉባቸው።

እነዚህን ምንባቦች በምታጠኑበት ወቅት የተጠቀሱትን ሌሎች ምንባቦች ደግሞ መጠናት ይኖርባችዋል።

## 7. የጥቅሶች ማውጫና አጠቃቀም

የምናጠናው ምንባብ የሚያብራሩትን ሌሎች ምንባቦች ከተቀረው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በአጠቃላይ ለማንበብ በምንሞክርበት ጊዜ መሪ ያስፈልገናል። እንደ አጋጣሚ ሆኖ ሁለት መሪዎች አሉን። እነርሱም በ1954 ዓ.ም በታተመው መጽሐፍ ቅዱስ ገርጌ የሚገኙት ማመሳከሪያ ጥቅሶችና የጥቅስ ማውጫ ናቸው። እነዚህን የእርዳታ ምንጮች እንዴት መጠቀም እንዳለብን መማር ይገባናል።

በመጽሐፍ ቅዱሳችሁ ውስጥ ታትሞ የምታገኙት የሚከተለው ነው:-

ሀ. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙት ማመሳከሪያ ጥቅሶች አጠቃቀም የሐዋ.16፡6-40ን ከፍታችሁ ተመልከቱ። በገጹ ግርጌ የሚገኙትን የማመሳከሪያ ጥቅሶች በማስተዋል ተመልከቱአቸው። ም የሚለው ፊደል ምዕራፍ ማለት ነው። የተጠቀሰው ምዕራፍ የዚሁ የመጽሐፍ ቅዱስ ነው። የሚከተለው በመጽሐፍ ቅዱሳችሁ ውስጥ ተጽፎ የምታገኙት ነው:-

16። 6፡7፥ ም8፡29። 14፤ ዮሐ.6፡44። 17፤ ማቴ.5፡7። 31፤ ም.15፡14፤ ዮሐ.3፡15። 37፤ ም22፡25። 39፤ ማቴ.8፡34

ይህም ማለት ምዕራፍ 16 ቁጥር 6-7። የሐዋ.8፡29ን ተመልከቱ።

- ቁጥር 14 ዮሐ.6፡44ን ተመልከቱ።
- ቁጥር 17 ማር.5፡7ን ተመልከቱ።
- ቁጥር 31 የሐዋ.11፡14ንና ዮሐ.3፡15ን ተመልከቱ።
- ቁጥር 39፡ ማቴ.8፡34ን ተመልከቱ ማለት ነው።

እነዚህ ማመሳከሪያ ጥቅሶች በሙሉ መታየት ይኖርባቸዋል። አንድ የማመሳከሪያ ጥቅስ ጠቃሚ መስሎ ከታየ በምንባቡ ቁጥር ጎን መመዝገብ ይኖርበታል።

ለ. የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ማውጫ አጠቃቀም።

ይህ መጽሐፍ ለመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ በጣም ጠቃሚ ስለሆነ አጠቃቀሙን ለማብራራትና በራሱ በመጽሐፉ ረዳትነት የትምህርት አስተዋፅዖችን ማዘጋጀት ለመለማመድ በዚህ ነገር ላይ ለሚያተኩሩ ሁለት ወይም ሦስት ትምህርቶች ሊሰጡት ይገባል። በእርሱ ውስጥ ቃላት

በቅደም ተከተል ስለተጻፉ የማውጫን አጠቃቀም ከመማራችን በፊት የአማርኛን ፊደላት በትክክለኛው ቅደም ተከተል መማር ይኖርብናል።

1. ከዚህ የሚከተሉትን ቃላት በትክክለኛ ቅደም ተከተላቸው ጻፉ። ትክክለኛው ቅደም ተከተል እንደዚህ መሆን አለበት ብላችሁ የጻፋችሁትን ዝርዝር በማውጫው ውስጥ ከሚገኘው ቅደም ተከተል ጋር በማመሳከር ልታርሙት ትችላላችሁ፦ ሰላም፥ ስንፍና፥ ስርየት፥ ሴት፥ ሰንበት፥ ሲዖል፥ ስድብ፥ ሰይጣን።

2. በብሉይ ኪዳን ለሲዖል የተሰጡትን የማመሳከሪያ ጥቅሶች በሙሉ ጻፉ። እያንዳንዱን ማመሳከሪያ ጥቅስ ከመረመራችሁ በኋላ የተጠቀሰው ጥቅስ እያንዳንዱ ቁልፉን ቃል የሚጠቀምበት መሆኑን እርግጠኞች ሁኑ።

3. የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት የሚገኙበት ቅደም ተከተል በቃላችሁ አጥኑ። የመጻሕፍቱ ዝርዝር በመጽሐፍ ቅዱሳችሁ መጀመሪያ ላይ ይገኛል።

## የክፍል ወይም የቤት ሥራ

1ኛ/ በሐዋ.5፡1-11 ውስጥ የሐናንያንና የሰጲራን ታሪክ አንብቡ። ከዚህ ምንባብ የምትማሩአቸውን እርግጠኛ የሆኑ ነገሮች ጻፉ።

2ኛ/ ከዚህ የሚከተሉትን ምንባቦች አንብባችሁ ታሪካዊ፥ ትምህርተ ሃይማኖት፥ ግጥም፥ ምሳሌ፥ ወይም ትንቢት ብላችሁ ከፋፍሉአቸው።
ማር.1፡14-15 ዘፀ.15፡1-19 1ኛ ነገ.15፡1-8 ዘፀ.20፡1-17 ሮሜ 11፡16-24 2ኛ ተሰ.4፡15-18

3ኛ/ ስርየት የሚለውን ቃል ከጥቅስ ማውጫ ፈልጋችሁ የቃላት አስተዋጽ አዘጋጁ። በብሉይ ኪዳን፥ በወንጌልና በጳውሎስ ደብዳቤዎች እንዴት እንደተጠቀሙበት ተመልከቱ።

# 8. መጽሐፍ ቅዱስን የመረዳት ዘዴ

ከመጽሐፍ ቅዱስ አንድ ምዕራፍ ወይም ምንባብ ከመረመርን በኋላ አሁንም የሚለውን በትክክል መረዳታችንንና የሚናገረውን ነገር ለማስተማር አስቀድመን ማረጋገጥ ያስፈልገናል። ለዚህም ስለ ምንባቡ ጥያቄዎችን መጠየቅና ትክክለኛ መልሶችን ለማግኘት መሞከር ይገባናል።

ይህ ክፍል በአጠቃላይ የሚያተኩረው ጥያቄዎችን በመጠየቅና መልሶቻቸውን በመፈለግ ላይ ነው።

*ሀ. ለማንኛውም ምንባብ የሚጠየቁ ጥያቄዎች*

አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ በምናነብበት ጊዜ መጠየቅ የሚገባ አንዳንድ ጥያቄዎች ከዚህ በታች ቀርበዋል።

1. ይህንን ምንባብ የጻፈው ማን ነው? ወይም ይህንን የተናገረው ማን ነው?

2. ይህንን የጻፈው ለማን ነው? ወይም ይህ የተነገረው ለማን ነበር?

3. ይህ ምንባብ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጨመረው ለምን ነበር?

ዮሐ.21፡25 በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያልተጻፉ ኢየሱስ ያደረጋቸው ብዙ ነገሮች እንዳሉ ይነግረናል። ስለዚህ ግልጽ በሆነ መንገድ የተጻፈው ነገር በተለይ ጠቃሚ ነው። ሁሉም የተጻፉት በዓላማ ነው።
ዘፀ.9፡13-16 እንደሚያሳየን እግዚአብሔር ለዓላማዎቹ ማስፈጸሚያ የማያምኑትንም እንኳ ይጠቀምባቸዋል።

በ2ኛ ሳሙ. 12፡1-23 ውስጥ የሚገኘው የዳዊትና ቤርሳቤህ ታሪክ ንሥሐም እንኳ የቅጣትን አስፈላጊነት እንደማያስወግድ ያሳየናል።

1ኛ ነገ.16፡34 ዘመን የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት እንደማይለውጣቸው ያመለክተናል። በኢያሱ ዘመን እስራኤላውያን ኢያሪኮን መልሰው እንዳይገነቡ ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው ሲሆን ከ350 ዓመታት በኋላ አኪኤል ያንን ትዕዛዝ ለመጣስ ስለደፈረ ተቀጥቶ ነበር።

4. የተጻፈው መቼ ነበር? ይህ በተለይ ምንባቡ በአዲስ ኪዳን ወይም በብሉይ ኪዳን ውስጥ እንደሆነ፤ ከክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ በፊት ወይም ከዚያ በኋላ እንደሆነ ለመገንዘብ ይጠቅማል። ለምሳሌ በብሉይ ኪዳን ዘመን አይሁዶች ቅዳሜን ማክበር ቢኖርባቸው ነገር ግን በአዲስ ኪዳን ክርስቲያኖች እሁድን ያከብራሉ።

5. ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ስለ እኔ ምን ይላል? ያስጠነቅቀኛል? ያበረታታኛል? አንድ ነገር እንዳደርግ ይጠቁመኛል? ወይስ ማድረግ የማይገባኝ ነገር? ልይዘው የሚገባኝ የተስፋ ቃል አለ? በቃሉ ላጠናው የሚገባኝ ጥቅስ አለ?

እንግዲህ እነዚህን ጥያቄዎች የምንጠይቅ ከሆነ መጽሐፍ ቅዱስን ስናስተምር ስህተቶችን እናስወግዳለን። ለምሳሌ መክ. 3፡19-20ን ተመልከቱ። ይህንን የተናገረው ማን ነው? የንጉሥ ዳዊት ልጅ ሰሎሞን ነበር፥ መክ.1፡1፤ 12። ይህንን የጻፈው ለምንድነው?

- በሰው ጥበብ ዕውቀትን ሁሉ ለማግኘት ስለ ሞከረ ነበር። ስለዚህ እርሱ የተናገረው የሰው ጥበብ እንጂ እግዚአብሔር የገለጸለት አልነበረም። ሰዎች ሁሉ በሚሞቱበት ጊዜ የሚሄዱት ወደ ተመሳሳይ ሥፍራ እንዳልሆነ እናውቃለን።!

ለ. ትክክለኛ መልሶቻችውን የማግኘት ዘዴ

አብዛኛውን ጊዜ ትክክለኛ መልሶቻችውን ከእነዚህ ከሦስቱ ሥፍራዎች ማለት ከመጽሐፍ ቅዱስ ከራሱ፤ ከመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያና ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ከተጻፉ መጻሕፍት ወይም ከእኛ የበለጠ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ከሚያውቅ ሌላ ክርስቲያን ልናገኛቸው እችላለን።

1. ከመጽሐፍ ቅዱስ

ከመጀመሪያ የመጽሐፍ ቅዱሱን ምንባብና በተጨማሪ እርሱን ለማብራራት የሚረዱትን ሌሎች ምንባቦች በከፍተኛ ጥንቃቄ ማንበብ ያስፈልገናል። አንድን ምንባብ በትክክል እንድንገረዳው የተቻለንን ያህል ማንኛውንም ማመሳከሪያ መመልከት እንደሚያስፈልገን አስቀድመን አይተናል። በተጨማሪ እያንዳንዱንም ቃል መመልከት ያስፈልገናል። የእያንዳንዱን ቃል ትርጉም እናውቀዋለን? ለምሳሌ በመግትና በክርክር መካከል ያለው ልዩነት ምንድንነው? 1ኛ ቆሮ.6፡1፤ 1፡11። በሚገባ እንደተረዳን እርግጠኞች ከሆንን ማድረግ የሚገባን ምንድነው? መልካም፤ በመጀመሪያ እንጸልይ። መጽሐፍ ቅዱስን የጻፈው እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ሲሆን እርሱ ራሱ ደግሞ ወደ ዕውነት ሁሉ እንደሚመራን ኢየሱስ ቃል ገብቶአል፥ 2ኛ ጴጥ.1፡20-21፥ ዮሐ.16፡13። በራሳችሁ ዕውቀት አትደገፉ፥ ምሳሌ 3፡5።

አሁንም የምንባቡን ትርጉም በትክክል መረዳታችሁን ፍጹም እርግጠኞች ካልሆናችሁ የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ እትሞችን ወይም በሌላ ቋንቋ የተጻፈውን ለማንበብ ሞክሩ። በርከት ያሉ ጥሩ የእንግሊዝኛ ትርጉሞች ቢኖሩ የኦሮሚኛና የትግሪኛ መጽሐፍ ቅዱሶችም አሉን። አዲስ ኪዳን በብዙ የተለያዩ ቋንቋዎች ተተርጉሟል።

2. ከመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ ወይም ከሌሎች መጻሕፍት

የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ ወይም መዝገበ ቃላት በምትጠቀሙበት ወቅት እነዚህ መጻሕፍት የተጻፉት በሰዎች መሆኑን አስታውሱ። እንደ እግዚአብሔር ቃል ስህተት የሌለባቸው አይደሉም። ነገር ግን ይበልጡን ጊዜ ጠቃሚ ናቸው። ለምሳሌ ስለ መገናኛው ድንኳን የሚነገረንን ዘጸ. 25-26 የምታጠኑ ከሆነ «ክርስቶስ በማደሪያው ድንኳን» የተባለውን መጽሐፍ ማንበብ ያስፈልጋችሁ ይሆናል። የምታጠኑት ከዕንባቆም ወይም ከሰፎንያስ ውስጥ ከሆነ «አስራ ሁለቱ ነቢያትና መልዕክቶቻቸው» ከተባለው መጽሐፍ ማንበብ ሊያስፈልጋችሁ ይችላል።

የምታጠኑት ከሐዋርያት ሥራ ውስጥ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የጻፈውን መልዕክት የሚመለከት ከሆነ፥ 2ኛ ቆሮ.7፡8፤ «የጳውሎስ ሕይወት፥ አገልግሎትና ትምህርቱ» ከተባለው መጽሐፍ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ስለጻፋቸው መልዕክቶች ማንበብ ሊያስፈልጋችሁ ይችላል።

የምታነቡት ኢየሱስ በሉቃስ 19፡41-44 ስለተነበየው ስለ ኢየሩሳሌም አወዳደቅ ከሆነ «የአዲስ ኪዳን ታሪካዊና ባህላዊ መሠረቶች የተባለውን መጽሐፍ አንብቡ።

3. ከሌላ ክርስቲያን

አንድ ሰው በጣም የተማረ ቢሆንም እንኳ አማኝ ካልሆነ በስተቀር ምናልባት በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታችሁ ሊረዳችሁ አይችልም። ይህም የሆነበትን ምክንያት ጳውሎስ ሲተነትን መንፈሳዊ ዕውነቶችን መረዳት የሚቻለው በመንፈስ ብቻ እንደሆነ ይናገራል፣ 1ኛ ቆር. 2፡14። ከሌላ ሰው የምታገኙት መልስ ዘወትር ሰውዬው ራሱን ለመንፈስ ባስገዛበት መጠን የተወሰነ እንደሆነ አስታውሱ።

## የክፍል ወይም የቤት ሥራ

1ኛ ለምን? ማን? ምን ማለት ነው? የሚሉትን ጥያቄዎች ከሚከተሉት ምንባቦች ውስጥ መልሱ። ሉቃስ 10፡1-12፣ ምሳሌ 30፡24-28 በተጨማሪ ቁ. 1ንም ተመልከቱ፣ ሕዝ.33፡30-33፣ ራዕይ 1፡10።

2ኛ ዮሐ.3፡1-15፣ ዮሐ.7፡45-52ና ዮሐ.19፡38-42 በጥንቃቄ መርምራችሁ ስለ ኒቆዲሞስ የምታገኙአቸውን አዳዲስ ነገሮች በሙሉ ጻፉ።

3ኛ የሚከተሉት ቃላት ትርጉም ምንድነው? ቤዛ፣ ዋጀ፣ ሳምራዊ፣ ጣር፣ መለከት፣ መላዕክት፣ ማስተሰሪያ።

# 9. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ምልክት የማድረግ ዘዴ

## መግቢያ

መጥረጊያ በጣም ንጹሕ ተደርጎ ቢጠበቅና ቆሻሻ እንዳይነካው ቢደረግ ምንም ጥቅም አይሰጥም። ጉራዴ ከአፎቱ ወይም ከማሕደሩ ወጥቶ በጦርነት ላይ ጥቅም ካልሰጠ በስተቀር አገልግሎት የለውም። መዶሻ ከመቀመጫ ስፍራው ተወስዶ ምስማር ለመምቻ በጥቅም ላይ ካልዋለ በስተቀር መዶሻ መግዛት ጨርሶ አያስፈልገንም። መጥረጊያ፣ ጉራዴና መዶሻ የተሠሩት ለመገልገያ ነው። እያንዳንዳቸው ያረጁና በጥቅም ላይ መዋላቸውን የሚጠቁም ምልክት ያሳያሉ። እንደ መጥረጊያ ወይም መዶሻ የኛም መጽሐፍ ቅዱስ በጥቅም ላይ ማዋሉን የሚጠቁም ምልክት ሊያሳይ ይገባል። መጽሐፍ ቅዱስ የተገዛው በጨርቅ ተጠቅልሎ በሳጥን ውስጥ እንዲቀመጥ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ የተገዛው ሊነበብ፤ ከውስጡ አውጥቶ ለማስተማር፤ ለሌሎች ለማሳየትና ለመጠናት ነው። ብዙ አስተማሪዎች መጽሐፍ ቅዱሳቸውን በጣም ስለሚጠቀሙበት በየዓመቱ አዲስ መጽሐፍ ቅዱስ መግዛት ያሻቸዋል።

መጽሐፍ ቅዱሶቻችንን በምናጠናበት ጊዜ በተለይ ጠቃሚ መስለው በሚታዩን ጥቅሶች ላይ ምልክት ማድረግና ቢያስፈልግም በገጾቹ ጠርዞች ላይ ማስታወሻ መጻፍ በጣም ይረዳናል። ይህ በጥንቃቄ ከተደረገ በምታስተምሩበት ወቅት መጽሐፍ ቅዱሳችሁ በጣም ይረዳችኋል። መንፈስ ቅዱስ አንድ ቀን የሚያስተምራችሁ ትምህርቶች በሚቀጥለው ቀን አይረሱም። ይህ ክፍል መጽሐፍ ቅዱሳችሁን በተለይም አንድ ምዕራፍን በምታጠኑበት ጊዜ እንዴት ምልክት ማድረግ እንደምትችሉ ጥቂት ፍንጮችን ይሰጣችኋል።

## ልንጠቀምባቸው የምንችላቸው አንዳንድ ምልክቶች

ሀ. በምዕራፉ ውስጥ እጅግ ጠቃሚ የሆነውን ጥቅስ ከሥሩ ልናሰምርበት እንችላለን። ጥቅሱ በጣም ረጅም ከሆነ ከጥቅሱ ግራና ቀኝ ጎን ሁለት ቀጥታ መስመሮች ማስመሩ ይመረጣል።

ለ. የምዕራፉን ቁልፍ ቃላት ዙሪያቸውን ልንከባቸው እንችላለን። አንዳንድ ጊዜ ለአጠቃላዩ ምዕራፍ አንድ ቁልፍ ቃል ብቻ ይኖረዋል፤ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ምናልባት ሁለት ቁልፍ ቃላት ይኖሩ ይሆናል። ሁለት ቁልፍ ቃላት የሚኖሩ ከሆነ አንዱን ዙሪያውን ስንከበው ሌላውን ግን በአራት ማዕዘን መስመሮች ብናጥረው የተሻለ ነው። ዕብ.11 ተመልከታችሁ እምነት የሚለው ቃል እያንዳንዱን ምልክት አድርጉበት።

ሐ. በአንድ ምዕራፍ ውስጥ አንድ ቃል ወይም ሐሳብ ከተደጋገመ በቀጥተኛ መስመሮች እናያይዛቸው።

መ. በምዕራፉ ውስጥ አንድ ጥቅስ ወደ ሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የሚጠቁም ከሆነ የብሉይ ኪዳን ማመሳከሪያ ጥቅሶችን በአዲስ ኪዳን ገጽ ግርጌ ተጽፈው እናገኛለን። ስለዚህ ጥቅሱንና ማመሳከሪያውን በድርብ መስመር ብናገናኛቸው ጠቃሚ ነው። ማቴ. 15፡8። ሉቃስ 20፡17ና 42 ተመልከቱ።

ሠ. በምዕራፉ ውስጥ ዝርዝር ነገሮች ከተሰጡ ቁጥራቸውን በቶሎ ለማወቅና ምናልባትም በእነርሱ ላይ አጭር ትምህርት ለመስጠት እንዲያመቾን ቁጥር ብንሰጣቸው የተሻለ ነው። ስለ አንድ ጳጳስ ባሕሪ 1ኛ ጢሞ.3፡2-4፡12 ተመልከቱ።

ረ. በቤታችሁ በምታጠኑበት ወቅት ዘወትር መጽሐፍ ቅዱሳችሁን በተለያዩ ቀለማት ምልክት ብታደርጉ ይረዳችኋል። እንደዚህ የምታደርጉ ከሆነ እያንዳንዱ ቀለም መወከል ያለበት ልዩ የሆነ ትምህርት ነው። ቀይ ማንኛውንም መስዋዕትን የሚመለከት ነገር መወከል አለበት። ብጫ መንግሥተ ሰማይን የሚመለከት ማንኛውንም ነገር መወከል አለበት። አረንጓዴ ትንቢትን መወከል አለበት ሰማያዊ ስለ ኃጢአት የሚናገሩትን ምንባቦች የሚወክል ቢሆን የተሻለ ነው።

## የክፍል ወይም የቤት ሥራ

1ኛ ቆር.ምዕ.1ን በአንድነት እንመርምር። በመጀመሪያ ባልገባን ቃል በእያንዳንዱ ላይ ምልክት እያደረግን ቢያንስ ምዕራፉን ሁለት ጊዜ ማንበብ አለብን። በቅድሚያ በምዕራፉ ውስጥ የተጠቀሱትን ሰዎች በሙሉ አስተውሉ። ስለ እያንዳንዳቸው ተጨማሪ መረጃ የምታገኙት የት እንደሆነ በትክክል ተረዱ። ለዚህ መረጃ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ጠቃሚ ነው።

ሶስቴንስ፡- የሐዋ.18፡7 ተመልከቱ።

አጵሎስ፡- የመጽሐፍ ቅዱስ መምህር፣ የሐዋ.18፡24።

ቀርስጶስ፡- በቆሮንቶስ የምኩራብ መሪ፥ የሐዋ.18፡8።

እስጢፋኖስ፡- በቆሮንቶስ የቤተ ክርስቲያን መሪና ጳውሎስን ከጎበኙት ከሦስቱ ሽማግሌዎች አንዱ፥ 1ኛ ቆሮ.16፡15።

ቀሎዔ፡- በቆሮንቶስ የነበረ አንድ አማኝ፥ 1ኛ ቆሮ.1፡11
ኬፋ፡- ጴጥሮስ ነው፥ ዮሐ.1፡42።

ጋይዮስ፡- በቆሮንቶስ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ምናልባት የምትሰበሰበው በእርሱ ቤት ሳይሆን አይቀርም፥ ሮሜ 16፡23።

# 10. ንድፎችን የመንደፍ ዘዴ

## መግቢያ

ንድፍ የምንጠቀመው ስለ አንድ ትምህርት ሰፊ መረጃ ሲኖረንና በጣም አጭር ግምገማ ማድረግ ስንፈልግ ነው። ንድፍ በተለይ ጠቃሚ የሚሆነው ዓረፍተ ነገሮችን በስዕሎች መተካት ስንችል ወይም በነገሮቹ መካከል ያለው ዝምድና የጊዜ ዝምድና የሆነ እንደሆነ ነው። ስለዚህ ከክርስቶስ መመለስ ጋር የተያያዙት ድርጊቶች እጅግ በጣም ግሩም በሆነ መንገድ በንድፍ ተገልጸዋል፤ ደግሞም የሥላሴ ትምህርት ብዙውን ጊዜ በንድፍ አማካይነት ይብራራል።

መጽሐፍ ቅዱስን ለማስተማር አብዛኛውን ጊዜ የንድፎችን ዕርዳታ ማግኘት በጣም ጠቃሚ ነው። ይህም ካርታዎችን፥ የዘመን ቅደም ተከተል ንድፎችን፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት አስተዋፆዎችንና ወዘተ ሊያጠቃልል ይችላል።

## የንድፍ አዘገጃጀት

ሀ. ንድፍ የመረጃ ግምገማ ሊሆን ይገባል፤ ስለዚህ ዋና ዋና ነገሮች ብቻ በውስጡ ሊጠቃለሉ ይገባል። ንድፉ በጣም ብዙ መረጃ ከመያዙ የተነሳ ገላጭ ከመሆን ይልቅ አደናጋሪ እንዳይሆን ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል። ከመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሱትን ጥቅሶች በሙሉ በንድፉ ውስጥ ከመጻፍ ይልቅ አብዛኛውን ጊዜ ማመሳከሪያዎችን ብቻ መጻፍ ይበቃል።

ለ. የንድፉ አቢይ ዓላማ በሁለት መንገዶች መታወቅ ይኖርበታል።
1. ከንድፉ አርዕስት
2. ከንድፉ ገጽታ።

አንድ ንድፍ ተጠቃሚው አጠቃላይ መዋቅሩን ተመልክቶ ወዲያውኑ በሚረዳው አኳኋን መዘጋጀት ይኖርበታል። በውስጡ ተጨማሪ የሆነ ጥቃቅን ሐሳቦች በመግባት መሠረታዊውን ይዘት አደናጋሪ እንዳያደርጉት ይገባል።

ሐ. አብዛኛውን ጊዜ አንድን መጽሐፍ ወይም ምዕራፍ ለማብራራት ነገሮቹን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባሉት ቅደም ተከተል ለማስቀመጥ ንድፍ ማዘጋጀት አማራጭ የሌለው ነው። ይህ አጠቃላይ መመሪያ ሲሆን የብሉይ ኪዳንን የጊዜ ቅደም ተከተል ንድፍ በምናዘጋጅበት ጊዜ ግን መዝሙረ ዳዊት ከእዝራና ነህምያ በፊትና ሚክያስ ከኤርምያስ በፊት ይሆናሉ።

መ. ለንድፍ ተስማሚ የሆነ አንድ ዓይነት ቅርጽ የለም። የዘመን ቅደም ተከተል ንድፎች አብዛኛውን ጊዜ አንድም ወይም ቀጥተኛ ናቸው፤ ትምህርተ ሃይማኖት ንድፎች ግን ክብ ወይም ሦስት ማዕዘን ወይም ደግሞ በይበልጥ ማንኛውም ተስማሚ የሆነ ሌላ ቅርጽ ያላቸው ሊሆኑ ይችላሉ። ማንኛውንም ዓይነት ቅርጽ እንምረጥ ሆኖም ቅርጹን የሚያመለክቱት መስመሮች በጣም ጉልህና ግልጽ መሆን ይኖርባቸዋል።

## የተለያዩ ዓይነት ንድፎች

ሀ. ካርታዎች

በካርታው ውስጥ ብዙ ነገሮች ለማስቀመጥ አትሞክሩ። እንደዚያ ካደረግን ካርታውን ለማንበብ አስቸጋሪ ይሆናል። በካርታው ውስጥ ማመሳከሪያዎችን መጨመርና ቁጥሮችን መጻፍ መልካም ሲሆን ማመሳከሪያዎቹን በካርታው መክፈቻ ውስጥ በገርጌ ወይም በስተ ጎን አስቀምጡአቸው።

ለ. የመለኮታዊ ትምህርት ንድፍ

ሐ. የትምህርተ ሃይማኖት ንድፍ

መ. የመጽሐፍ ጥናት ንድፍ /ለምሳሌ በአዲስ ኪዳን መክፈቻ ውስጥ የሚገኙትን ንድፎች ተመልከቱ።/

# 11. የቃላት ጥናት

መጽሐፍ ቅዱስን የምናጠናበት አንዱ መንገድ ቃላትን ማጥናትና መጽሐፍ ቅዱስ እነዚህን ቃላት እንዴት እንደተጠቀመባቸው መመርመር ነው። ልናጠናቸው የምንፈልጋቸው አንዳንድ ቃላት ለምሳሌ ከዚህ በታች ቀርበዋል። እነዚህም ቃላት አንዳንዶቹ መልክዓ ምድራዊ፣ የሕይወት ታሪክ ነክና መለኮታዊ ትምህርት ነክ ናቸው።

ሀ/ መልክዓ ምድር ነክ የሆኑ ቃላት ጥናት

የአካባቢው ካርታና የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ስለ እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ሥፍራዎች ብዙ መረጃዎችና ዕውቀት ይሰጣችኋል።

1. ግብፅ
2. ኢትዮጵያ
3. ሲናና ብዙ ሌሎች ሥፍራዎች።

መልከዓ ምድራዊ ቃላቶችን በምናጠናበት ጊዜ ከዚህ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ራሳችንን መጠየቅ ያስፈልገናል፦

1. ይህ ስፍራ ወይም ወንዝ ወይም ተራራ የሚገኘው የት ነው?
2. በዚያ ሥፍራ ምን ተደረገ? በብሉይ ኪዳን/በአዲስ ኪዳን?
3. በትንቢት ተጠቅሶ ነበር?
4. ስሙ ትርጉም አለው?
5. ለእግዚአብሔር ሕዝብ መልካም ሥፍራ ነበር? ወይስ መጥፎ?
6. ስለ ክርስትና ሕይወት ምን ያስተምረኛል?

ለ/ የሕይወት ታሪክ ነክ የሆኑ ቃላት ጥናት

ስለምታጠኑት ሰው የሕይወት ታሪክ የምታገኙትን ማንኛውንም ማመሳከሪያ ዝርዝር ለመጻፍ ሞክሩ። እነዚህ ነገሮች በሁለት ክፍሎች ይከፈላሉ።

1. በሕይወቱ ዋና ዋና ድርጊቶች ላይ የሚያተኩሩ አቢይ ምንባቦች።
2. አልፎ አልፎ ስለ እርሱ የተሰጡ ተጨማሪ መረጃ ጥቅሶች ወይም አንዳንድ አስተያየቶች።

<u>ማሳሰቢያ</u>፦ ስለ አንድ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስላለ ሰው የሚናገሩትን ጥቅሶች በሙሉ ለመፈለግ የመጽሐፍ ቅዱስን የጥቅስ ማውጫ በምንጠቀምበት ጊዜ ጥቅሶቹ የሚያመለክቱት <u>ይህንን ሰው ራሱን</u> እንደሆነ አስረግጦ ማወቅ በጣም ጠቃሚ ነው። ለምሳሌ ያዕቆብ ተብለው የተጠሩ አራት የተለያዩ ሰዎች አሉ።

ሀ. የዮሐንስ ወንድም፥ ማቴ. 4፡21
ለ. የእልፍዮስ ልጅ፥ ማቴ. 10፡3
ሐ. የጌታችን ወንድም፥ ገላ.1፡19
መ. የይሁዳ ወንድም፥ ሉቃ.6፡16

በሕይወት ታሪክ ጥናቶች ውስጥ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ ይኖርብናል፦

1. የስሙ ትርጉም ምንድነው?
2. ወላጆቹ እነማን ናቸው? ወንድሞቹና እህቶቹ እነማን ነበሩ?
3. አይሁዳዊ ከሆነ፤ የየትኛው ነገድ ተወላጅ ነው?
4. የኖረው የት ነበር?
5. የኖረው በየትኛው ዘመን ነበር?
6. ያገባው ማንን ነበር?
7. ልጆቹ እነማን ነበሩ?
8. ዋና ተግባሩ ምን ነበር?
9. ሕይወቱ ስለ ክርስትና አኗኗር ምን ያስተምረኛል?

ሐ. መለኮታዊ ትምህርተ ነክ የሆኑ ቃላት ጥናት

እንደዚህ ዓይነቱ ጥናት ከመልከዓ ምድራዊ ወይም ከሕይወት ታሪክ ጥናቶች የበለጠ በጣም አስቸጋሪ ነው። አብዛኛውን ጊዜ በቤ/ክ ስብሰባዎች ውስጥ ተሰሚ አይደለም፤

ለመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪው ለራሱ ግን በጣም ጠቃሚ ነው። ብዙውን ጊዜ በዕለታዊ ኑሮአችን የማይጠቅሙን ብዙ ቃላቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይገኛሉ። ለምሳሌ እንደ ቅዱስ፥ ጻድቅ፥ ድህንነት፥ ትንሳኤ፥ ወንጌል፥ ፀጋ፥ ቃል ኪዳንና ... ወዘተ የመሳሰሉት ቃላት።

በዚህ የቃላት ጥናት ውስጥ የመጀመሪያው እርምጃ ቃሉ እንዴት በጥቅም ላይ እንደዋለ ማስተዋል ሲሆን አንዳንድ ጊዜም ቃሉ በጭራሽ በሥራ ላይ ያልዋለበትን ሁኔታ መመልከት ጠቃሚ ነው። ለምሳሌ ቅዱስ የሚለውን ቃል።

ስለ መለኮታዊ ትምህርት ቃላት ጥናት የቃላት ጥናት መጽሐፍ ተመልከቱ።

## የክፍል ወይም የቤት ሥራ

1ኛ የቃላት ጥናት አዘጋጁ።

- ስለ ኢየሩሳሌም
የዮሐንስ ራዕይ ስለ ኢየሩሳሌም የሚያስተምረው ትምህርት ምንድነው? ራዕ.21፡1-4።

- ስለ ያዕቆብ
እግዚአብሔር ኤሳውን ትቶ ያዕቆብን የመረጠው ለምንድነው? ሮሜ 9፡6-16።

2ኛ ስለ ትንሳኤ። በክርስቶስ ትንሳኤ፥ በመጀመሪያው ትንሳኤና በ2ኛው ትንሳኤ ላይ የተለየዩ ጥናቶችን አድርጉ።

3ኛ ሀ. የኡር ከተማ የምትገኘው የት ነበር? የምትገኝበትን ሥፍራ ለማሳየት ቀላል ካርታ ሳሉ።
ለ. የአብራም አባት ማን ነበር?
ሐ. የስምዖን ጴጥሮስ ወንድም ማን ነበር?
መ. መና ምንድነው?
ሠ. የጢሞቴዎስን እናትና አያት ስም ጻፉ።

# 12. የመጽሐፍ ጥናቶች

አንድን መጽሐፍ አስቀድማችሁ ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ በጥንቃቄ ካላጠናችሁትና የመጽሐፉን አጠቃላይ አስተዋፅዖ በሚገባ ሳታውቁ ለማስተማር ሙከራ ማድረግ ተገቢ አይደለም።

የመጀመሪያው ተግባራችሁ መሆን ያለበት ተማሪዎቻችሁ አስተዋፅዖውን መረዳታቸውን ማረጋገጥ ሲሆን ከዚያም በኋላ ሁኔታውን ተመልክታችሁ ዝርዝር ነገሮችን ማስተማር ትችላላችሁ። በአዲስ ኪዳንና በብሉይ ኪዳን መክፈቻ ውስጥ የመጽሐፍ አስተዋፅዖዎችን ተመልከቱ።

በተለይ ሁሉም ክፍሎች እኩል ርዝመት እንደሌላቸው አስተውሉ። አንዳንድ ጊዜ አንድ አጠቃላይ ትምህርት ጥቂት ቃላት ብቻ ያስፈልጉታል ወይም በአንድ ትምህርት ላይ ሁለት

ምዕራፎችን ወይም የበለጠ ልናጠፋ እንችል ይሆናል። <u>የሚቻል ከሆነ በአንድ ትምህርት ወይም ስብከት ውስጥ ልናስተምረው የወሰንነው ክፍል አንድ ነጠላ ዓላማ ሊኖረው ይገባል።</u> በአንድ ትምህርት ውስጥ ብዙ አቢይ ትምህርቶችን ለማስተማር ስንሞክር የትኛውም በአድማጮቹ ሊጨበጥ አይችልም።

ማንኛውንም የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ ከማስተማራችን በፊት በተቻለ መጠን የመጽሐፉን መሠረታዊ ነጥቦች ለማግኘት መጣር ይኖርብናል። ልንጠይቃቸው የሚገቡን አንዳንድ ጥያቄዎች ከዚህ በታች ቀርበዋል፡-

ሀ. ይህንን መጽሐፍ ማን ጻፈው?

ለ. የተጻፈው ለማን ነበር? ለአይሁዶች ነው? ለክርስቲያኖች ነው?

ሐ. የተጻፈው ከየት ነበር? ተቀባዮቹስ የት ነበሩ?

መ. የተጻፈው ለምን ነበር? ለማበረታታት? ለመገሰፅ? ለማስተማር?

ሠ. የተጻፈው መቼ ነበር?

<u>ለምሳሌ</u>፡- ጳውሎስ የገላትያን መልዕክት ጽፏል። ይኖሩ የነበሩት በትንሹ እስያ ነበር። የተጻፈው ጳውሎስ ከመታሠሩ በፊት ሲሆን ምክንያቱ ለመዳን መገረዝና ሕግን መጠበቅ ያስፈልጋል የሚለውን የሐሰት ትምህርታቸውን ለማስተማር አንዳንድ ሐሰተኛ መምህራን ወደ ገላትያ መሄዳቸው ነው። የጳውሎስ መልዕክት ይህ ነገር ትክክል እንዳልሆነ ያሳያል። የጳውሎስ ሕይወትና ትምህርቱ ተመልከቱ።

## <u>13. ትምህርት ለማስተማር መዘጋጀት</u>

ማስተማር በስሎ ተዘጋጅቶ የቀረበ ምግብ ማደል አይደለም። ትምህርቶች መታቀድ ያስፈልጋቸዋል።

ትምህርት ለማስተማር ስንዘጋጅ የሚከተሉትን ነገሮች ማስታወስ አለብን፡-

ሀ/ አቢይ ትምህርቱን መምረጥ

ቃሉ በሚገኝበት ምዕራፍ ወይም አንቀጽ ውስጥ ከአንድ በላይ ትምህርት ሊኖር ይችላል። በአዕምሮአችን ውስጥ የያዝነውን አንድ የተወሰነ ትምህርት ቢኖረን የተሻለ ነው። ትምህርቱ የተወሰነ ካልሆነ ከአንዱ ርዕስ ወደ ሌላው ስንቃኝ እኛን ለማዳመጥ የመጣው ሕዝብ አንድም ነገር ሊያስታውስ አይችልም።

ለ/ የትምህርቱን ዓላማ ማዘጋጀት

በመጀመሪያ የትምህርታችንን ዓላማ እናቅድ፤ ይኸውም ለማድመጥ የመጡት ሰዎች እንዲማሩትና ከተማሩት ነገር የተነሳ እንዲያደርጉ የምንፈልጋቸው ነገሮች ማዘጋጀት ይኖርብናል።

ትምህርቱን በምናዘጋጅበት ወቅት ይህንን ዓላማችንን በአዕምሮአችን መያዝ ይገባናል። እያንዳንዱ የትምህርቱ ክፍል ከዓላማችን ጋር መዛመድ አለበት።

መልካም ዓላማ አጭር ቢሆን ከአድማጮችም መልስ ማግኘት የሚፈልግ ነው፤ ይኸውም የአቋም ለውጥ ከእግዚአብሔር ቃል ስለተነገረው እውነት አንድ ነገር ለማድረግ የመሄድ ፍላጎት ሊሆን ይችላል።

ሐ/. የትምህርቱን መግቢያ ማዘጋጀት

የመግቢያው ዓላማ የአድማጮችን ሐሳብ አንድ አቅጣጫ እንዲይዝ መሰብሰብ ነው። አጭር ምሳሌ ወይም ታሪክ፤ ጥቂት ጥያቄዎች ወይም ወቅታዊ የሆነ ድርጊት ማቅረብ ሐሳባቸውን ሊሰበስብ ይችላል። ነገር ግን ያ ታሪክ ወይም ጥያቄዎቹ ልናስተምረው ካሰብነው ትምህርት ጋር የሚዛመድና ወደዚያው አቅጣጫ የሚመራን መሆኑን እርግጠኞች ሁኑ።

መ/. የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት

ይህ የእግዚአብሔር ቃል ስለሆነ የትምህርቱ ዋና ክፍል ነው። የመጽሐፍ ቅዱስን ዕውቀት ብቻ እንዳናስተላልፍ ቃሉ የሰዎችን ልብ እንዲነካ ጸልዩ። ትምህርቱ የምናስተምራቸውን ሰዎች መንፈሳቸውን የሚያሳድግና ችግራቸውን የሚያቃልል እንዲሆን ጸልዩ።

ሠ/. መደምደሚያ

የትምህርቱን ፍሬ ነገርና የእግዚአብሔርን ቃል መመሪያ በምናጠቃልልበት ወቅት ተጨባጭ አድርገን ከሕይወት ሁኔታዎች ጋር እንዴት እንደሚገናዘብ ማሳየት ይኖርብናል። እግዚአብሔር ኑሮአችንን እንዲመራ የሰጠን ቃሉን እንደሆነ ተማሪዎችን አሳስባቸው።

የማስተማር ዘዴና «አገርዋና ቤትዋ» በሚሉት መጻሕፍቶች የሚገኙ ትምህርቶች በዚህ ክፍል ውስጥ የተጠቀሱትን ነጥቦች ያብራራሉ።